የባህላዊ አዳኝና የሚታዊ ተጋዳሊ ጉዞ እጣዎች ንጽጽራዊ ትንተና፤ በመለየት ፈለግ መነሻ

A Comparative Analysis of the Traditional Hunter and the Mythic Hero's Departure Journey

ለማ ንጋቱ ታረቀኝ[1] እና ሙሉ ጌታቸው መንግስቱ[2]

Lemma Nigatu Tarekegn and Mulu Getachew Mengistu

አህጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት መሰረታዊ ግብ በሚታዊ ተጋዳሊና በባህላዊ አዳኝ የህይወት እጣ ጉዞዎች የሚታዩ ተመሳስሎዎችንና ልዩነቶችን በማነጻጸር የፎክሎር ጥናት ትንተና ለሁለንተናዊነት (universality) እና አካባቢያዊነት (locality) ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ አይነታዊ ሲሆን ኢትኖግራፊያዊ የምርምር ንድፍን ተከትሏል፡፡ ለጥናቱ ከምስራቅ ወለጋ ዞን፣ ኪረሙና ጉድሩ፤ ከኢሉ አባቦር ዞን፣ ቡሬ፤ ከጅማ ዞን፣ ሰኮሩ ወረዳ በታላሚ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ በእነዚህ ወረዳዎች ከሚኖሩ የተጠኚው ማሕበረሰብ አባላት መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ነው፡፡ በቃለ መጠይቅ የተሳተፉት 24 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሲሆኑ፣በቡድን ውይይት ደግሞ 23 የባህሉ እውቀት ያላቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡ ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊዎች የተመረጡት በታላሚ እና በጓድ ጥቆማ የንሞና ዘዴዎች ነው፡፡ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰነዶች ከአብያተ መጻሕፍትና ከሌሎችም ቦታዎች ተሰብስበዋል፡፡ የመረጃዎቹን ምሉዕነትና ትክክለኝነት የማጣራት ስራ ከተከናወነ በኋላ በመለየት ምእራፍ ስር በሚገኙት አምስት ንዑሳን ምዕራፎች ስር ተመድበው ትንተናው ተካሂዷል፡፡ የጥናቱ ውጤትም፣ በገድል ጥሪ፣ ጥሪውን ለመቀበል በሚኖር ፈቃድ (እምብኝታ)፣ በልእለ ተፈጥሮ ረድኤት፣ የመጀመሪያውን እና የመጨረሻውን ቅጽሮች በመዝለቅ፣ በሚታዊ ተጋዳሊና በባህላዊ አዳኝ የእጣ ጉዞዎች መካከል ተመሳስሎ መኖሩን አሳይቷል፡፡ በእነዚህ ምእራፎች ስር ያሉ ዝርዝር ጉዳዮች ሲታዩ ግን፣ በሚታዊ ተጋዳሊና በባህላዊ አዳኝ የዕጣ ጉዞዎች መካከል ባህል ፈጠር ልዩነቶች ታይተዋል፡፡ ይህም የፎክሎር መረጃዎችን ለሁሉም ባህሎች በሚሰራው በሁለንተናዊነት ወይም የየባህሎች ተናጠናላዊ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ በሚያተኩረው አካባቢያዊነት ላይ ብቻ ተመስርቶ መተንተን ጥናቱን የተሟላ እንደማያደርገው ያሳያል፡፡ ስለሆነም የጋራ አካዳሚዊ ዕውቀቶችን ለማዳበርና የየባህሎችን ተናጠላዊ ጉዳዮች ለመረዳት ለሁለቱም ተገቢው ትኩረት ቢሰጥ መልካም ይሆናል፡፡

ቁልፍ ቃላት፡- መለየት፣ ሚት፣ ባህላዊ አዳኝ፣ ተጋዳሊ፣ ጉዞ

---

[1] ፒ.ኤች.ዲ. ተ/ፕ፣ ዋና ተመራማሪ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ-አማርኛ ት/ት ክፍል፣ ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡- drlemma.nigatu@ju.edu.et lemmanigatu@gmail.com

[2] ፒ.ኤች.ዲ ረ/ፕ፣ ረዳት ተመራማሪ፣ ጅኦግራፊና የአካባቢ ጥበቃ ት/ት ክፍል፣ ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡- mulur2010@gmail.com, mulu.getachew@yahoo.com

Abstract

The primary objective of this study is to underscore the necessity of integrating both universality and locality in folklore analysis. By conducting a comparative examination of the mythic hero's and the traditional hunter's life journeys, this research highlights their shared motifs as well as culturally distinct variations. Employing a qualitative ethnographic approach, the study focuses on selected communities in Kiramu and Guduru (East Wollega Zone), Bure (Ilu Aba Bor Zone), and Sokoru *Woreda* (Jimma Zone). Data were systematically collected through in-depth interviews with 24 key informants and focus group discussions involving 23 culturally-knowledgeable participants. Participants were selected using a combination of purposive and snowball sampling techniques to ensure depth and relevance. Supplementary archival materials were also gathered from libraries and other relevant sources. Following a rigorous verification process to ensure data accuracy and completeness, the findings were organized into five analytical subsections. The study reveals striking parallels between the mythic hero's journey and that of the traditional hunter, particularly in key stages such as: the call to adventure; the acceptance (or refusal) of the call; the intervention of supernatural aid, and the symbolic crossing of thresholds (both initial and final). However, a closer examination of these stages uncovers culturally specific variations, demonstrating that neither a purely Universalist (cross-cultural) nor an exclusively localist (culture-specific) approach suffices for a comprehensive understanding of folklore. Thus, this study advocates for a dual analytical framework—one that balances universal archetypes with local particularities—to advance scholarly discourse and foster a deeper appreciation of both shared narrative structures and unique cultural expressions.

Keywords: myth, traditional hunter, hero, journey

መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ

በፎክሎር የዘውግ ምደባ፣ በንደፈ ሐሳብ ብልጸጋና በእነዚህ ላይ ተመስርቶ በሚካሄደው ትንተና በሁለት ጎራዎች የሚካሄዱ የንድፈ ሐሳብ ክርክሮች ይታያሉ፡፡ አንደኛው ጎራ፣ የሰውን ልጅ የጋራ ሥነልቡናዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች ማሳየት ላይ ሲያዘነብል፣ ሁለተኛው እንደየባህሉና ሁኔታው ተለዋዋጭ የሆኑት እሴቶችና ህጎች ላይ ያተኩራል፡፡

እነዚህ ሁለት ተቃራኒ ጎራዎች[3]፣ የተቀነቀኑት በዋና ዋና ቅርጾች ንደፈ ሐሳቦች (the theory of primary forms) እና በታሳቢ አይነቶች ንድፈ ሐሳቦች (the theory of ideal types) ተከታዮች ነው (ብርሃኑ 1995፣21፣ Finnegan 1992፣25፣ Green 1997፣ 411)። ቅርጽ ላይ አትኩረው በዳበሩት ንደፈ ሐሳቦች፣ የባህል እድገት አንድ አቅጣጫዊ ተደርጎ ይታል። ይህ አመለካከት ቀደም ሲል በዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሐሳብ (evolution theory) በአሁኑ ጊዜ በእድገት 'development' እና በዘመናዊነት 'modernisation' ፍልስፍናዎች ይንጸባረቃል (ፊኔጋን 1992፣25)። በፍልስፍናዎቹ ባህል ሁለንተናዊ (universal) ተደርጎ ስለሚታይ በምዕራባውያን ሥነ ቃሎች ባህርያት መነሻነት የሌሎችን ሥነ ቃሎች መተንተን የተለመደ አሰራር ነው።

በተለያዩ ባህሎች መካከል የሚገኙ ሥነ ቃሎችን ግንኙነቶች እና የሰው መሆንን ምንነት ገልጦ በማሳየት ከሌሎች የሰብዐዊ ሳይንስ ሙያ ዘርፎች በላይ ትኩረት በሚሰጠው በፎክሎር የዕውቀት መስክ ለሁለንተናዊነት ልዩ ትኩረት ይሰጣል (Wilson 1988፣157)። የጆሴፍ ካምቤልን እና የዴቪድ ሊሚንግን መጻሕፍት የጋራ ትኩረት የመረመሩት ቴዎድሮስ (2001) ‹‹ሚቶች፣ ከጥቅሉ የሰው ልጅ ህልውና ጋር ተቆራኝተው አስተሳሰቡን እየመሩ፣ አነጋገሩን እየገሩ፣ ድርጊቱን ጭምር እየተጫኑና እየቀረጹ ዛሬን እንደዘለቁ›› መግለጻቸው ለሁለንተናዊ ተግባራቸው ማሳያ ይሆናል።

በፎክሎር ጥናት ምደባም ሆነ ትንተና እንዲህ አይነት የጋራ ጉዳዮች ላይ አትኩሮ ለአያሌ ዘመናት ሲሰራበት የኖረው ንጽጽራዊ/ሁለንተናዊ አወጋገን ባለንበት ዘመን በገጠመው ጠንካራ ንድፈ ሐሳባዊ ሙግት ምክንያት ተመራማሪዎች የባህሉ ባለቤቶች ስለራሳቸው ጥበባዊ ስራዎች ያላቸውን አመለካከት መመርመር ላይ ማትኮር መያዛቸውን ብርሃኑ (1995፣22) ይገልጻሉ። በዚህ መንገድ የሁለንተናዊ አመለካከት ተቃራኒ ሆነው ብቅ ያሉት የእስብ አይነቶች ንድፈ ሐሳብ አራማጆች፣ የፎክሎር/ሥነ ቃል ዘሩን፣ ይዘት፣ ቅርጽ፣ ስልት፣ መዋቅር፣ ተግባር፣ መከሰቻ፣ ስርጭት፣ ዕድሜ እና ከየት መጣ መነሻ በማድረግ፣ የፎክሎር ቅርጹ ባለቤት የሆነው ማኅበረሰብ በሚረዳበት አካባቢያዊ/ቀያዊ አረዳድ መመደብና መተንተን ተገቢ መሆኑን መግለጻቸውን ፊኔጋን (1992፣25) እና ብርሃኑ (1995፣22) ይገልጻሉ።

እነዚህ ሁለት ተቃራኒ ንድፈ ሐሳባዊ አመለካከቶች በጥቅሉ ሲታዩ፣ የሰው ልጅ የጋራ ጉዳይ ላይ ከመመስረት ወይም የየባህል ልዩነቶች ላይ ከማትኮር ይመነጫሉ። የፎክ ቡድኖች ማንነት መገለጫ የሆነውን ሎርን (ባህልን) በሰው መሆን የጋራ ባህርያት መነጽር ብቻ መመልከት ወይም የሰውን ልጅ የጋራ ጉዳይ ወደጎን በመተው ከእያንዳንዱ ባህል ተናጠላዊ ባህሪ ላይ ተመስርቶ መመደብም ሆነ መተንተን የፎክሎርን ጥናት የተሟላ እንደማያደርገው መረጃዎች ያሳያሉ። ለምሳሌ በSims እና Stephens (2011) ስለፎክሎር ተግባር (ገጽ፣181)፣ መዋቅር (ገጽ፣

[3] Green ዋና ዋና ቅርጾችን ሁለንተናዊ (universal) ሲሏቸው፣ ብርሃኑ ንጽጽራዊ ወይም ሉላዊ ይሏቸዋል። ታሳቢ አይነቶች፣ በይዘታቸው፣ በቅርጻቸው፣ በስልታቸው፣ በተግባራቸው፣ በድግግሞሻቸው፣ በእድሜቸውና በከየትመጣቸው የተለዩ፣ ቀያዊ ናቸው (Green፣ Finnegan፣ ብርሃኑ)

189/90) እና ፍካሬ ልቡና (ገጽ፣196) በቀረቡት ንድፈ ሐሳቦች፣ የጋራ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ የተለያዩ ባህሎችንና የፎክሎር ዘሮችን በስፋትና በጥቅል ለመተንተን የተደረጉ ጥረቶች የየንድፈ ሐሳቦቹ ቀርነቶች ተደርገው መጠቀሳቸው፣ መረጃዎችን ከሁለንተናዊነት አቅጣጫ ብቻ ማየት የሚያስከትለውን ክፍተት ያሳያል፡፡ ዝርዝር አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ማትኮርም፣ የሙያ ዘርፉን ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ እድገት የመገደብና ተጠኚው ማኅበረሰብ የራሱ ባህል ላይ ብቻ እንዲያተኩር (ethnocentric) የማድረግ አንድምታ ይኖረዋል፡፡

የፎክሎርን የብሄርተኝነት ስሜት የወደፊት ተግዳሮቶች የመረመሩት አብርሃም (1994፣149)፣ ከእኛ ባህል ውጭ የሆኑ የሌሎች ባህሎችን ስናነጻጽር የሚያለያዩን ገጽታዎች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ሰው ሆኖ በመወለድ በጋራ የሚያስተሳስሩን ላይም ማትኮር እንደሚገባ መግለጻቸው፣ አንዱን አቅጣጫ ብቻ መከተል የሚያጎድለው ነገር መኖሩን ያሳያል፡፡ የየባህሉ ተናጠላዊ ሎሮች የእያንዳንዱን ሀገር ማንነት በትክክል መግለጻቸውን እንደምንረዳው ሁሉ፣ ሰው የመሆንን የጋራ ምንነት ለመረዳት እንደሚያግዙ መገንዘብ እንደሚገባንም ያስገነዝባሉ፡፡

ከነአብርሃም (1994) ሐሳብ፣ በፎክሎር ጥናት ለሁለንተናዊነትና አካባቢያዊነት ሚዛናዊ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህን ሚዛናዊነት በመጠበቅ የተካሄዱ የሀገር ውስጥ የፎክሎር ጥናቶችን የዚህ ጥናት አቅራቢዎች ከአብያተ መጻሕፍትና ከድረ-ገጾች ባደረጓቸው አሰሳዎች ለማግኘት አልቻሉም፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ከተለያዩ ባህሎች በተሰበሰቡ ሚቶች የጋራ ባህርያት ላይ የተካሄደውን የቴዎድሮስን (2001) መጣጥፍ በማንጸሪያነት በመውሰድ፣ የደቡብ ምዕራብ ኦሮሞ ማኅበረሰብ የባህላዊ አደን ልማድን በመተንተን በዘርፉ የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት ጥረት ተደርጓል፡፡

1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሚታዊ ተጋዳሊና በባህላዊ አዳኝ የመለየት ጉዞዎች መካከል የሚታዩትን ተመሳስሎዎችና ልነቶች በንጽጽር መተንተን ነው፡፡ በንኡስነት ደግሞ በሚታዊ ተጋዳሊና በባህላዊ አዳኝ የህይወት እጣ ጉዞዎች የሚታዩ ልዩነቶችና ተመሳስሎዎች የፎክሎርን ሁለንተናዊነት (universality) እና አካባቢያዊነት (locality) እንዴት እንደሚያሳዩ ይተነትናል፤ አንድምታዎቻቸውንም ይገልጻል፡፡

2. የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

ተጋዳሊነት እንደየባህሉና እንደየዘመኑ አስተሳሰብ ሊተረጎሙ የሚችሉ የተለያዩና ሰፋፊ ሐሳቦችን የያዘ ጽንሰ ሐሳብ ነው (Goldberg፣ 2009፣1)፡፡ Jayawickreme እና Di Stefano (2012) ተጋዳሊነትን እንዴት ልናጠናው እንችላለን? የሚለውን ጥያቄያቸውን ለመመለስ ከመረመሯቸው ውስን ጥናቶች መካከል፣ የCarlyle (2001 [1841]) በዓለም ታሪክ ራሳቸውን ለታላቅነት ያበቁ ስመጥር ሰዎች፤ የCampbell (2004 [1949] ከምሥጢራዊ ዓለም ለወገኖቹ (ተከታዮቹ) ክብር ከሚያስገኝ በረከት ጋር የተመለሰ፤ የOliner (2002) ሌሎችን ለመታደግ ራሱን በፈቃዱ ለአደጋ ያጋለጠ እና የFeatherstone (1992) ከተለመደው የተረጋጋ ዓለም በተለየ፣ መከራ፣

ብጥብጥና ስቃይ በተጋረጠበት ህይወት የሚኖር፣ በሚሉት የጽንሰ ሐሳቡ ብያኔዎች ዙሪያ ስምምነቶች መኖራቸውን ይገልጻሉ፡፡

Klappም (1954፣58) በተጋዳሊነት መገለጫ መልኩ ድል አድራጊ ጀግና፣ ብልህ (ከጉልበት ይልቅ በብልሃት የሚያሸንፍ)፣ አሳሽ ወይም ጠያቂ ተጋዳሊ፣ ታዳጊ ተጋዳሊ፣ በጎ አድራጊ ተጋዳሊ፣ ባህላዊ ተጋዳሊና ሰማዕታዊ ተጋዳሊ በህይወት ወስጥ በስፋት የሚመላለሱና የተለመዱ፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በድራማና በፎክሎር ሁለንተናዊነት ነስተው የሚሰየሙ ጭብጦች መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ Vogler (2003) በሚታዊ ተጋዳሊና በፊልሞች ገጸባህርያት የታሪክ ጉዞ ምእራፍ መዋቅሮች መካከል ተመሳስሎ እንደሚታይ ማረጋገጣቸው፣ ከዚሁ ከሁለንተናዊነት የጋራ ባህርይ ለመፍለቁ ማሳያ ይሆናል፡፡

Jayawickreme እና Di Stefano ደግሞ፣ ጀግንነት (Heroism) - አንድ ግለሰብ ለተቀደሰ ተግባር ያለውን ቁርጠኝነት፣ አብዛኛውን ጊዜ የሌሎችን ደህንነት ለመጠበቅ ያለመና ዓላማውን ለማሳካት የሚገጥሙትን ፈተናዎች ለመቀበል ያለውን ፈቃደኝነት እንደሚያካትት በመግለጽ፣ በከፊልም ቢሆን የOlinerን (2002) ብያኔ ይጋራሉ፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣488) ጀግናን፣ ‹‹ለሀገር ለወገን መስዋእትነት ከፍሎ ጥሩ ተግባር አከናወነ፣ ወኔ፣ ድፍረት በሚጠይቅ ሁኔታ ላይ ጀብዱ የሰራ፣ ብርታት፣ ጥንካሬ የሚጠይቅ ሥራ ላይ ችግርን ተቋቁሞ ለውጤት የበቃ ጎበዝ›› በማለት ከላይ ከቀረቡት ብያኔዎች በሚቀራረብ መልኩ ይበይነዋል፡፡ Propp (1984፣149) የሶቪየት ህብረትን የጀግና መወድሳዊ ግጥሞች ምንነት በመረመሩበት ጽሑፋቸው፣ የጀግና ወመድሳዊ ግጥም (epic) ትግልና ድል (struggle and victory) በይዘትነት የሚነሳበት የጀግንነት ውስጣዊ መገለጫ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት ሀሳቦች፣ የጀግንነት ምንነትና መገለጫዎች በተለያዩ ባህሎች በጋራ ይዘትነት እንደሚነሱ ያሳያሉ፡፡ የጋራ ይዘት መኖሩ ግን የጀግኖቹን ገድል ወጥና ተመሳሳይ ሊያደርገው አይችልም፡፡ ልዩነቶቹ ባህላዊ እሴቶች ከውስጣቸው የሚፈልቁ ጀግኖችን ድርጊቶችና አመለካከቶች ከመቅረጻቸው ይመነጫል (Lowrey፣ 2009፣1)፡፡

የሰው ልጅ የጋራ ሁለንተናዊ እሴቶችም ሆኑ የባህሎች የየግል አሻራዎች፣ ከየባህሎቹ ተግዳሮቶችን ለማስወገድ፣ የየባህሎቹን የጋራ ርዕዮች ከፍ ለማድረግ፣ ክብር ለመስጠት ወዘተ. በሚቀረጹት የሥነ ጽሑፍ፣ የፊልም፣ የሚት፣ የአፈታሪክ ወዘተ. ተጋዳሊ ገድሎች ውስጥ ይንጸባረቃሉ፡፡

በሚንጸባረቁባቸው ዓላማዎችና መንገዶች ግን ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ ለልዩነቶቹ መከሰት ምክንያት ከሚሆኑት ውስጥ ርእዮተ ዓለማዊ ፍልስፍናዎች ተጠቃሽ ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ በኢሴንሻሊዝም ፍልስፍና፣ የግለሰብም ሆነ ግለሰቦች የሚፈጥሯቸው ቡድኖች ተረኮችም ይባሉ ማንነቶች በተፈጥሮ የሚወረሱና ዘላቂነት ያላቸው የየማኅበረሰብ ወጥ የእሴት ሥርዓቶች ተደርገው ስለሚወሰዱ (Childs & Fowler፣ 2006) የጀግንነት እሴቶችም የሚወረሱ[1] እና ቋሚ ተደርገው ይታያሉ፡፡

ይህንን አመለካከት በሚቃረነው ድኅረ ዘመናዊ አንጻራዊነት (postmodern relativism) ፍልስፍናዊ እይታ፣ የሚደጋገፉም ሆነ አብረው የማይሄዱ የተለያዩ ርዕዮተዓለማዊ ጉዳዮች እንደ ኢሴንሻሊዝም በወጥነት ወይም ሁለንተናዊነት ሳይሆን በተለያዩ አማራጮች ሊመረመሩ እንደሚገባ ስለሚታመን (Sedrakyan፣ 2023) የጀግንነት እሴቶች እንደያውዱ በተለያዩ መንገዶች ስለሚታዩ ቋሚ ብያኔዎች ቦታ የላቸውም፡፡

የእነዚህ ፍልስፍናዎች ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ ‹‹ዛሬውን ዘንግቶ የትናንት እሴቶችንና ሥርዓቶችን እያቀነቀነ በሚኖረው በብሉይ ሚቶሎጂ እና ለዚህ ሚት ‹‹ፍጹማን›› እውቅና በመንፈግ የግለሰብን ልቡና እና ዩኒቨርሳዊ ቁርኝት ልማዱ በሚያደርገው ሀዲስ ሚቶሎጂ›› መሃከል በግልጽ ይታያል፡፡ ‹‹ከመደበኛ ሃይማኖቶች በተቃራኒ፣ ከተገዳድፎ ይልቅ የተደጋግፎን እሴቶች የሚያጸና ቢሆንም፣ አዲሱ ተጋዳሊ ከቀደምቱ ተጋዳልያን የተቀዳ፣ … ተረኮቻችንም ነባሮቹ እሴቶች ባደሩባቸው ቀደምት ተረኮች እርሾነት የተበጁ በመሆናቸው›› (ቴዎድሮስ፣ 94/5) በተቃርኗቸው ውስጥ የሚጋሯቸው ጉዳዮች ያሏቸው መሆናቸውን ያሳያሉ፡፡

ይህ በተራዛሚው ስለትናንት የጀግንነት መገለጫዎችና እሴቶች ስናነሳና የዛሬውንም ሆነ የነገውን መገለጫዎቹንና የሚያጸናቸውን እሴቶች ስናስብ፣ ቋሚ ባህርይ ይዞ ሊዘልቅ አለመቻሉን፣ እንደ አውዱና ፍልስፍናው ስለሚለዋወጥ ልዩነቶች አይቀሬ መሆናቸውን ያስገነዝባል፡፡ በልዩነቶቹ ውስጥ የሚመዘዙ የጋራ አስተሳሳሪ ባህርያት መኖራቸውንም እንደዚሁ፡፡

ይህም የኢሴንሻሊዝም በሁለንተናዊ እውነታ ወይም የጋራ ባህርያት ኑረት ላይ ማመን፣ የድኅረ ዘመናዊ አንጻራዊነት በእውነታ መንታዊነት፣ ተለዋዋጭነት፣ ግለሰባዊነትና ሁኔታዎች ላይ ተመስራችነት ላይ ማትኮር፣ በሁለቱ ፍልስፍናዎች መሃከል መሠረታዊ ተቃርኖ መኖሩን ያሳያል፡፡ Potgieter & Van der Walt (2015) እንደሚገልጹት ይህ ተቃርኖ በየራሳቸው መታየት እንጂ አንዳቸው በሌላኛቸው መዳኘት እንደሌለባቸው ያስገነዝባል፡፡ የሚያገናኗቸው የተወሰኑ ነገሮች ቢኖሩም በመሠረታዊነት የተለያዩ ናቸውና፡፡

የሚት ተጋዳሊን ዕጣ ጉዞ ከፎክሎር ቴክስቶች ጋር እያነጻጸሩ መተንተን እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ Finnegan (2012፣202) የጦርነትና የአደን ቃል ግጥሞች ቀጥተኛ የርእሰ ጉዳይ ግንኙነት ባይኖራቸውም፣ ሁለቱም ከተለመደው የዕለት ተዕለት ተግባር ውጭ የሆኑ ድርጊቶችን ማካተትን፣ አደጋን መጋፈጥን፣ ድልን ወይም ጀግንነትንና ግለ-ገድልንና ልዩ ችሎታን ማንሳታቸው እንደሚያመሳስሏቸው ይገልጻሉ፡፡

Rankም (2015፣2) የሚታዊ ተጋዳሊንና የባህላዊ ጀግናን የዕጣ ጉዞ ተመሳሳይነት መርምረዋል፡፡ ምስስሎሹ፣ እንደ እብራውያን፣ ግብጻውያን፣ ሮማውያን ወዘተ. አይነቶቹ የቀደምት የስልጣኔ ባለቤቶች፣ ሀገራዊ ጀግኖችንና አፈታሪካዊ ነገሥታትን የሚያከብሩ ሚታዊ አፈታሪክ ሥነ ጽሑፎችን ማበርከታቸውና ሚቶቹ በስፋት መሰራጨታቸው ለኋለኞቹ የሀገራዊ ጀግና ትረካዎች መሠረት በመጣላቸው እንደተፈጠረ ይገልጻሉ፡፡

Evansም (2018፣12) የሚታዊ ተጋዳሊ ጉዞ ሰፊ ስርጭት እንዳለውና ከጥንታዊ ሚቶች ነፍስና ስጋ ነስቶ፣ የጋራ ችግሮች፣ ጉዞዎች፣ እና የጀግንነት ድርጊቶች ላይ ባነጣጠሩ ዘመናዊ ተረኮች መገለጫዎችን እያሰረጸ በአዲስ አውድ እንደሚከሰት በመግለጽ የራንክን ሐሳብ ይጋራሉ፡፡

ቴዎድሮስም (2001፣59-60) የሚታዊና የባህላዊ ተጋዳልያንን ወደ ኅብረት የሚያመጣው አንድ የጋራ ሁነት ‹‹ጉዞ›› መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ የጉዞ መሠረታዊነት በሚት ዓለም ውስጥ ብቻ ያልተገደበና ከሰው ልጅ ህልውና ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ሕይወታዊ ክስተት መሆኑን በመግለጽም የሰው ልጅና የሚታዊ ተጋዳልያን ጉዞዎች ተመሳስሎ የሚመነጨው ከሚያልፉባቸው እጣዎች ተመሳስሎ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ከጉዞ በተጨማሪ የሚታዊ ተጋዳሊም ይሁን የባህላዊ ጀግና የመጨረሻ ድሎች በሥርዓቶች መታጀባቸውም ያመሳስላቸዋል (Sims እና Stephens 2011፣95)፡፡ የሚታዊ ታጋዳሊና የባህላዊ ጀግና የጉዞ እጣዎች መመሳሰል፣ የሰው ልጅ ሰው በመሆን የጋራ ባህርይም ይባል ነገሮች ባላቸው ተመሳስሎ፣ የጋራ ክንውኖችና አስተሳሰቦች መገለጫዎች መኖራቸውን ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል የሰውን አስተሳሰብና ድርጊት ፈር የሚያስይዙት የተለያዩ ባህሎችና አካባቢዎች የሚያሳርፏቸው የየራሳቸው አሻራዎች ልዩነቶችን ይፈጥራሉ፡፡ ሁለንተናዊነትንና አካባቢያዊነትን (ልዩነት) የሚያሳዩት መረጃዎች፣ ከሁለቱ ጉዞዎች ዝርዝር ንጽጽሮች እንዴት እንደሚመዘዙ በትንተናው ክፍል ቀርቧል፡፡

3. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ አይነታዊ ሲሆን ኢትኖግራፊያዊ የምርምር ዘዴን ተከትሏል፡፡ ለጥናቱ ከምስራቅ ወለጋ ዞን፣ ኪረሙና ጉድሩ፤ ከኢሉ አባቦር ዞን፣ ቡሬ፤ ከጅማ ዞን፣ ሰኮሩ ወረዳ ተመርጠዋል፡፡ ወረዳዎቹ የተመረጡት በዞኖቹ ውስጥ ከሚገኙት ሌሎች ወረዳዎች በበለጠ የቡድን አደን በስፋት ሲካሄድባቸው የነበሩ በመሆናቸው የተሻሉ መረጃዎች እንደሚገኙባቸው በመታመኑ ነው፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን በመያዛቸው የተመረጡት መጻሕፍትና የጥናት መጽሔት ደግሞ፣ ከቴዎድሮስ (2001) - ‹‹ብሉይ ሚቶሎጂ››፣ ከCampbell (2004) - ‹‹The Hero with A Thousand Faces››፣ ከGoldberg (2009) - ‹‹The Hero’s Journey›› እና ከVan Gennep (1960) - ‹‹The Rites of Passage›› ናቸው፡፡

የመስክ መረጃዎቹ በአደን ተግባር ካለፉና በዚሁ ተግባራቸው ማዕረግ ካገኙ ቁልፍ መረጃ አቀባዮችና ስለአደን ማሕበራዊና ባሕላዊ ፋይዳ ከሚያውቁ በሂደቱ ካላለፉ ነዋሪዎች ተሰብስበዋል፡፡ ሁሉም የመረጃ ምንጮች የተመረጡት በዓላማ ተኮር (purposive) እና የጓድ ጥቆማ (snowball) የንሞና ዘዴዎች ነው፡፡ የመስክ መረጃዎቹ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ሲሰበሰቡ፣ የሰነዶቹ ደግሞ በሰነድ ፍተሻ (document analysis) ተሰብስበዋል፡፡

ለቃለ መጠይቁ፣ ከፊል ነጻ የሆኑ መነሻ ጥያቄዎች (Semi-structured interview guide questions) ተዘጋጅተው አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በቃለ መጠይቅ መረጃ

የሰጡት 24 ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሲሆኑ፣ ሁሉም ቃለ መጠይቆች በቴፕ ተቀድተው ወደ ጽሑፍ ተቀይረዋል፡፡ ለቡድን ተኮር ውይይቱ መነሻ የሆኑ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ሁለቱንም ጾታዎች ያካተቱ፣ ከስድስት እስከ ስምንት ተሳታፊዎች የተገኙባቸው ሶስት የቡድን ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን፣ የጠቅላላ ተሳታፊዎች ቁጥር 23 ነው፡፡

በሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ደግሞ፣ ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ የአደን ጉዳይን በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ካካተቱ መጻሕፍትና ሌሎች ሰነዶች፣ በየወረዳዎቹ የአካባቢና የዱር እንስሳት ጥበቃ ጽሕፈት ቤቶች ከተዘጋጁ መጽሔቶች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ከምርምር መጽሔቶችና ሌሎችም ግለሰባዊ ሰነዶች የተገኙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አስችሏል፡፡

የሚታዊ ተጋዳሊንና የባህላዊ አዳኝን የጉዞ እጣዎች መረጃዎች ለመተንተን የGennep የሽግግር ንድፈ ሀሳብ (theory of rites of passage)፣ መነጠል (Separation) → (መሸጋገር) Transition እና → መጠቃለል (Incorporation) እና የCampbell የጀግና ጉዞ ዞሮ ገጠም የህይወት ኡደት፣ መለየት (separation)፣ መሸጋገር (initiation) መመለስ (return) እና የንጽጽራዊ አንጻር (comparative approach) ንድፈ ሐሳቦች ተመርጠዋል፡፡ የGennep እና የCampbell ንድፈ ሐሳቦች የተመረጡት Goldberg (2009፣9) እንደሚገልጹት፣ የተጋዳሊ ሚትን (hero myth) ይዘትና ውስጣዊ መዋቅር በንጽጽር ለማጥናት በር የከፈቱና የቴክስቶችን ጽንሰ ሐሳቦችና ባህርያት ለመተረክ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች በመሆናቸው ነው፡፡

ንጽጽራዊ አንጻርም በፎክሎር ጥናት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲሰራበት የኖረና አሁን ድረስ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ (Finnegan፣1992፣29)፣ የሚታዊ ተጋዳሊንና የባህላዊ አዳኝን የጉዞ እጣዎች ተመሳስሎና ልዩነት ለመተንተን በማስቻሉ ተመርጧል፡፡

በተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ የመረጃ ማጣራት ከተከናወነ በኋላ፣ ኮድ ተደርገው እንደየተመሳስሏቸው በመለየት (departure) ዋና ምዕራፍ ስር በሚገኙት አምስት ንኡሳን ምእራፎች፣ (የገድል ጥሪ፣ እምቢኝታ፣ የልእለ ተፈጥሮ ረድኤት፣ የመጀመሪውንና የመጨረሻውን ቅጽሮች መዝለቅ) ተመድበው በገለጻና በፍከራ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡

4. የመረጃ ትንተና

በዚህ ክፍል Campbell (2004 [1949]) በሚት የተጋዳሊው ዕጣ የሚጓዝባቸውን ፈለጎች፣ መለየት፣ መዝለቅ እና መመለስ መነሻ በማድረግ፣ ባህላዊ አዳኙ በሕይወት ሽግግር ከሚያልፍባቸው (በካምቤል ከገጽ 45-88 የቀረቡት) እጣዎች ጉዞ፣ ቴዎድሮስ (2001፣5) በመለየት ገናን ምእራፍ ስር ካቀረቧቸው አምስት ንኡሳን ምዕራፎች እየተስተያዩ አንድነታቸውና ልዩነታቸው ከሚከተለው ስለባህላዊ አዳኞች ማንነትና ስለባህሉ አውድ ፍንጭ ከሚሰጠው ጭምቅ መረጃ ቀጥሎ ተተንትኗል፡፡

ይህ ጥናት በተካሄደባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የኦሮሞ ማኅበረሰብ አባላት ለባህላዊ አደን ልዩ ትኩረት አላቸው፡፡ ልማዱ በአጠቃላይ በብሔረሰቡ ሰርጾ የኖረ ጥንታዊ ባሕላዊ ጉዳይ መሆኑን Zelalem (2003፡122) እና Bartels (1983፣ 255-286) ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ጥናት ባህላዊ አዳኝ ተብለው የተገለጹት ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ የሚኖሩ የኦሮሞ ማኅበራሰብ ወንድ አባላት ናቸው፡፡ በዚህ ማኅበረሰብ ለአቅመ አዳም የደረሱ ወንዶች፣ ያላገቡት ሚስት ለማግባት፣ ያገቡት ለራሳቸውና ለቤተሰባዊ ዘር ግንዳቸው ጭምር ማኅበራዊ ክብር ለማስገኘት፣ በረሃ ወርደውና ችግርን ተቋቁመው እንደ አንበሳ፣ ጎሽ፣ ዝሆን፣ ቀጭኔ ያሉትን ታላላቅ እንስሳት አድነው በመግደል ማህበራዊ ክብር የማግኘት ስር የሰደደ ባህል ነበራቸው፡፡

ወጣቶች በአካልና በመንፈስ ሲጠነክሩ ይህን ከባህላቸው የሚጠበቅ ግዴታ ስለሚያውቁ ለባህላዊ አደን ራሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ ትንሽ ዘግየት ካሉ፣ በማኅበራዊ መገለልና በሥነ ቃል ይተነኮሳሉ፡፡ ያላገቡት ለትዳር በሚጠይቁት ልጃገረድ፣ ያገቡት በሚስቶቻቸው እና አድነው በተመለሱ የማኅበረሰቡ አባላት ወደ አደን እንዲሄዱ ግፊት ይደረግባቸዋል፡፡

ትንኮሳውና ማኅበራዊ መገለሉ ሲበዛባቸው በመመካከር ለአደን ይነሳሳሉ፡፡ በቅድሚያ የአደን ልምድ ያለው አሳዳኝ ይመርጣሉ፡፡ አሳዳኙ የካበት የአደን ልማድ ዕውቀትና አስተባብሮ የመምራት ችሎታ ያለው ተሰሚ ግለሰብ መሆን ይኖርበታል፡፡ እሱን ከመረጡ በኋላ፣ የአደን ስንቅ እንዲያዘጋጁላቸው ለቤተሰቦቻቸው ይነግራሉ፡፡ እስከ 15 የሚደርሱ ጓደኛሞች ተስማምተውና ቀን ቆርጠው መሳሪያዎቻቸውንና ስንቃቸውን ያዘጋጃሉ፡፡

መልካሙ ሁሉ እንዲገጥማቸው በቤተሰብ ተመርቀው በዶሮ ጨኸት ወደ መረጡት በረሃ በመሄድ ማረፊያ ቦታ ያዘጋጃሉ፡፡ ተጠሪ፣ አዝማች፣ የተጠሪ ተወካይም ይመርጣሉ፡፡ በእነዚህ አመራር በእሳት (ንኡስ ቡድን) ደረጃ ይከፋፈላሉ፡፡ እንደ ብዛታቸው ከ3-5 የሚደርሱ እሳቶች ይኖሯቸዋል፡፡ ለማደን እጣ ሲወጣ፣ የየእሳቶቹ ተወካዮች ይገኛሉ፡፡ በበረሃ መከበር ያለባቸውን ሕጎች የሚያስከብርና ሲጣስ የሚቀጣም ይመርጣሉ፡፡ በዚህ መሠረት እያደኑ እድል የቀናቸው እየገደሉና በጓደኞቻቸው አስፈላጊው ጥበቃ እየተደረገላቸው ይሰነብታሉ፡፡ የመመለሻ ጊዜያቸው ሲደርስ፣ የገደሉት ወደ ቤተሰቦቻቸው ደግሰውና ተዘጋጅተው እንዲጠብቋቸው የምስራች ነጋሪ ይልካሉ፡፡

አዳኞቹ በድል ሲገቡ ክብት ይታረዳል፤ በአካባቢው የሚኖረው ሰው የሚበላና የሚጠጣ ይዞ ይሄዳል፤ ይጨፈራል፡፡ ቤተዘመድ ገዳዮችን ይሸልማል፡፡ ቀደም ብለው የገደሉት አዳኞች ተሰባስበው ጌረርሳ እያወረዱ እየተበላና እየተጠጣ ሁለት ሶስት ቀን ይጨፈራል፡፡ ገዳዮቹ ስላገዳደላቸው፣ ስላሳለፉት ውጣ ውረድ፣ ስለፈጣሪ እርዳታ እያነሱ ጌረርሳ ያወርዳሉ፡፡ አብረዋቸው የነበሩት ጓደኞቻቸው እውነት መሆኑን ይመሰክሩላቸዋል፡፡ የባህሉ ሥርዓት ከተከናወነላቸው በኋላ የአዳኝነት ማኅበራዊ ክብር ያገኛሉ፡፡ እድል ያልቀናቸው ለሌላ ጊዜ ይቀጥራሉ፤ በምን ይገፍ ልመልስ ወይም በአደጋ እንደወጡ የሚቀሩም አሉ፡፡

እድል የቀናቸው ከሰው በላይ ይቀመጣሉ፣ ሲናገሩ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡ ጌረርሳና ዘፈን ሲኖር እነሱ ይቀድማሉ፤ በማንኛውም ጉዳይ በአካባቢው ክብር ይሰጣቸዋል፡፡ አለባበሳቸው፣ የተለየ ነው፤ ጸጉራቸውን አሳድገው ያበጥራሉ፤ ቅቤ ይቀባሉ፡፡ የተለዩ ስለሆኑ ሰው ያከብራቸዋል፡፡ ምግብም ሆነ መጠጥ የሚቀርብላቸው በተመረጠ እቃ ነው፡፡ ሲሞቱ እንኳ መቃብር እስኪገቡ ፊታቸው ሳይሸፈን ይፈከርላቸዋል፡፡ ለስማቸው ማስታወሻም የገደሉትን እንስሳ ምንነት የሚያሳይ ምልክት፣ ማበጠሪያና መስተዋታቸው በባለባላ የወይራ ምሰሶ ላይ መንገድ ዳር ከፍ ተደርጎ (ፋቻ) ይሰቀልላቸዋል፡፡ ሚስትም ቀድማ የመናገር፣ ከሴቶች በላይ የመቀመጥ፣ ወረፋ ሳትጠብቅ ውሃ የመቅዳትንና ሌሎችንም ማኅበራዊ ክብሮች ታገኛለች፡፡ ቤተዘመዱም የአያት ቅድመ አያት ባህሉን አስከባሪ የአዳኝ ዘር በመሆኑ ይከበራል፡፡

ባህሉ፣ ባህላዊ አደን በህግ ከተከለከለበት ጊዜ ጀምሮ የቀነሰ ቢሆንም፣ በአንድ በኩል በሂደቱ ያለፉት አባቶች በሕይወት በመኖራቸው፣ በሌላ በኩል አጋጣሚዎችን እየጠበቁ በድብቅ የማደን ልማድ በመኖሩ፣ የጥናቱ መረጃዎች እስከተሰበሰቡበት እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ መረጃዎች በስፋት ይገኙ ነበር፡፡

ወደ ትንተናው ክፍል ስንገባ በመጀመሪያ ደረጃ የሚገኘው የሚታዊ ተጋዳሊና የባህላዊ አዳኝ የጉዞ እጣ፣ መለየት ነው፡፡

4.1. መለየት (Departure)

መለየት ከነበሩበት ቡድን መውጣትን ያሳያል፡፡ ቴዎድሮስ (2001፣5) እንደሚገልጹት፣ ሚታዊ ተጋዳሊው ከሚጓዝባቸው ፈለጎች የመጀመሪያው መለየት ነው፡፡ በመለየት ስር የገድል ጥሪ፣ እምቢኝታ፣ የልእለ ተፈጥሮ ረድኤት፣ የመጀመሪውን ቅጽር መዝለቅ እና የአሳ ነባሪ ከርስ (የመጨረሻውን ቅጽር መዝለቅ) ይጠቃለላሉ፡፡ የባህላዊ አዳኝ የመለየት ጉዞ ከእነዚህ ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

4.1.1. የገድል ጥሪ (The Call to Adventure)

ለሚታዊ ተጋዳሊውም ሆነ ለባህላዊ አዳኙ ከመለየታቸው በፊት የገድል ጥሪ ይደርሳቸዋል፡፡ ለሁለቱም ለረጅሙ ጉዞዎቻቸው ማስጀመሪያ የሚሆኑ የገድል ጥሪዎች በዘወትራዊዎቹ መኖሪያዎቻቸው የሚደርሷቸው መሆናቸው የጋራ ጉዳዮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የትግል ማስጀመሪያ የገድል ጥሪ ለሁለቱም ቢደርሳቸውም፣ በገድል ጥሪው፣ ዓለማ፣ አደራረስ፣ በአድራሾቹ ማንነትና እጩዎቹ ለጥሪው ምላሽ ለመስጠት በሚኖራቸው ነጻነት ጉልህ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ ለሚታዊ ተጋዳሊዎቹ ጥሪው በዱብእዳ መልክ ‹‹በነቢያት፣ በቅዱሳት፣ ባህሉ ባከበራቸው፣ የተለየ ክህነት ባላቸው ሰዎች ወይም በመላዕክት፣ በአማልክት አንደበት በሚነገር ቃል በትዕዛዝ መልክ ወይም በዕለት ተለት ኑሮ በሚፈጸሙ ድርጊቶች፣ በሕልም እና በራዕይም ሊደርስ ይችላል፡፡

ለባህላዊ አዳኞች የገድል ጥሪው የሚደርሳቸው እንደሚታዊ ተጋዳሊዎች፣ በድንገታዊ የመብረቅ ብልጭታ በትእዛዛዊ ዱብእዳ ሳይሆን፣ በትንኮሳ ቀስ በቀስና በተለመደ መንገድ ነው፡፡ የገድል ጥሪው የሚመጣውም እንደሚታዊ ጀግኖቹ በተለዩና ልዕለ ሰብእ ክብር ባላቸው አካላት ወይም በህልምና በራዕይ ሳይሆን፣ እንደነሱው ተራ በሆኑና የባህል ግዳጃቸውን በመወጣት በተከበሩ አዳኞች ውረፋ፣ በሚስቶቻቸው ወይም ለትዳር ባሰቧቸው ልጃገረዶች ንቀት፣ በሌሎች የማኅበረሰባቸው አባላት ትንኮሳ በአደን አነሳሽ ሥነ ቃሎች አማካይነት በግልጽና ፊት ለፊት ነው፡፡

ከገድል ጥሪ አድራሾቹ ማንነትና ከጥሪው አደራረስ ልዩነት በተጨማሪ፣ ሚታዊ ተጋዳሊዎችና ባህላዊ አዳኞች ለገድል በሚጠሩባቸው ዓላማዎችና የበቀሉበት ማኅበር ለገድል ጥሪዎቹ በሚኖረው አቋም ላይም ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ ለሚታዊ ተጋዳሊዎቹ ጥሪው የሚደርሳቸው በሚኖሩበት ማኅበር ወግና ልማድ ላይ እንዲያምጹ ነው፡፡ ‹‹በነባሩ ልማድና ሥርዓት ላይ የበቀለው ማኅበር…የቆየው እሴት ዘላለማዊነትን ያገኝለት ዘንድ ስለሚመኝ አዳዲስ አስተሳሰቦችን፣ ፍንገጣዎችን፣ አመጾችን ለማስተናገድ ፈጽሞ ፈቃደኛ ስለማይሆን…ለተጋዳሊው አመጽ የሚሰጠው ምላሽ አብሮ መኖርን ይከለክላል፤ የማይታረቅ ጸብን ይወልዳል›› (ቴዎድሮስ 2001)፡፡ ለባህላዊ አዳኞች የሚደርሰው የገድል ጥሪና የአቋመ ማኅበራቸው የገድል ጥሪ ምላሽ ከዚህ ፍጹም ተቃራኒ ነው፡፡ ለአዳኞቹ የገድል ጥሪው የሚደርሳቸው በበቀሉበት ማኅበረሰብ ወንድ ሁኖ በመወለድ አስቀድሞ በተወሰነ እጣ ፈንታ ገፊነት ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ሊያስቀጥላቸው የሚፈልጋቸውን እሴቶች፣ አዳኞቹ የድርሻቸውን ተወጥተው እንዲያስከብሩ ይጠብቃል፡፡ ይህን የማኅበር ባህላዊ ግዳጅ ችላ ሲሉ ወይም ለሌሎች ነገሮች ሲተጉ፣ የማኅበሩ አባላት በሥነቃሎቻቸው አማካይነት ግፊት ይፈጥሩባቸዋል፡፡

አድኖ ክብር ያገኘው የማኅበሩ አባል፣ በተለይ ያልገደሉት መርጠው የመልበስና እዩኝ እዩኝ የማለት ባህርይ ሲያሳዩ፣ በጌረርሳ በአደባባይ በህዝብ ፊት ክብራቸውን ይነሷቸዋል፡፡ ላላደኑት የገድል ጥሪ የሚሆንባቸው እንዲህ አይነቱ ምጸታዊ ውረፋ ነው፡፡

Bara baraan miiccattaa	በየዘመኑ ትታጠባለህ፣
Yaa wayyaa addeettii koo	አንተ ነጩ ልብሴ፣
Duutee nan obbaafattuu	አትገላገለኝ ሞተህ፣
Ajjeestee nama hin taatuu	ወይ ሰው አትሆን ገድለህ፣
Taa'ii na dhaggeeffadhu	አድምጠኝ ተዘርፍጠህ!
Yaa garaa baldheettii koo	ቻይ የሆንከው ሆዴ፡፡

የማኅበረሰቡ አባላት በተለያዩ መንገዶች የአደን ተግባርን ማበረታታት፣ አዳኞቹ የአያት ቅድመ አያቶቻቸውን ባህል እንዲያስቀጥሉ ያላቸውን ጽኑ ፍላጎት ያሳያል፡፡ ሚታዊ ተጋዳሊዎችም ሆኑ ባህላዊ አዳኞች የፈለቁባቸው ማኅበረሰቦች፣ ነባር ባህሎቻቸው ሳይነኩና ሳይበጠበጡ ባሉበት እንዲቀጥሉ መፈለጋቸው

ያመሳስሏቸዋል፡፡ ልዩነቶቻቸው የሚመነጨት የባህላዊ ተጋዳሊዎቹ ማኅበር አቋም፣ ተጋዳሊዎቹ ነባሩን ባህል ከሚጥስ የገድል ጥሪ እንቅስቃሴያቸው እንዲታቀቡ ማድረግ ሲሆን፣ የባህላዊ አዳኞቹ ማኅበር አቋም፣ ነባሩን ባህል ከዘነጋ ዝምታቸው እንዲነቁ ከማነሳሳት መመንጨታቸው ነው፡፡

ለሚታዊ ተጋዳሊው ጥሪው በሚቀርብበት ወቅት የ‹‹አጠቃላዩን የሰው ልጅ የመኖር ምክንያት ከገዛ ራሱና ከማኅበሩ የኑሮ ዘይቤ ጋር እያነጻጸረ ገምግሞ ለተጋድሎ በተመቻቸ የስሜትና የልቡና ሁኔታ በመገኘት ጥሪውን ተቀብሎ ጉዞ ለመጀመር ዝግጁ እንደሚሆነው ሁሉ›› (ቴዎድሮስ 2001፣7)፣ አዳኙ በማኅበረሰቡ አማካይነት የገድል ጥሪ ሲደርሰው የስሜትና የአዕምሮ ዝግጁነት ይዞ መገኘቱ ያመሳስላቸዋል፡፡

ለባህላዊ አዳኙ፣ በአዳኞች፣ ለጓደኝነት ባሰባት ሴት ወይም በሚስቱ በሚገጠሙበት የትንኮሳ ቃል-ግጥሞች ገፊነት፣የገድል ጥሪ ሲደርሰው፣ የባህሉን ግዴታ ለመወጣት ልቡ መቁረጡን፡-

Booreen narra guutuu dha	ቁጭቴ እጅግ ብዙ ነው፣
Kan booree bahe korma	ቁጭቱን የተወጣው ጀግና ነው፡፡
Oromummaan Kitila	ኦሮሞነት ሚሊዮን ነው፣
Booree baadheen gidira	እንከራተታለሁ በልቤ ቁጭት ይገፍ፡፡
Yaa barii ji'aa hin jenne	አላልኩም ነጋ አልነጋ፣
Yaa marii firaa hin jenne	አልሄድኩም ምክር ፍለጋ፡፡
Gaafichan kana yaade	ይህን ያሰብኩኝ ዕለት፣
Kilaashii koo fudhadhe	ክላሼን አነሳሁት፡፡
Balbala koo dhungadhe	የቤቴንም በር ሳምኩኝ፣
Du'aaf garaa kutadhe	ለሞት ሆዴን ቆረጥኩኝ፡፡

እያለ አድኖና ገድሎ ባለመግባቱ ከነገዱ መነጠሉንና ይህም እጅግ ለሚያሳቅቅ ሀፍረት የዳረገው መሆኑን ጌረርሳ አውርዶ ትግሉን ይጀምራል፡፡

የሚት ተጋዳሊ ጥሪውን የተቀበለ ሰው እውነተኛ ተጋዳሊነቱን ለማስመስከር በቅድሚያ በገዛ ራሱ ላይ ከሰለጠነና ራሱን ካሸነፈ በኋላ፣ በራሱ ፈቃድም ይሁን በልዕለ ተፈጥሮ ኃይሎች ጫና ገድሉን ለመፈጸም ወደ አንድ የማይታወቅ፣ የሚፈራና የሚጠላ ጨለማ ዓለም እንደሚዘልቀው ሁሉ፣ ባህላዊ አዳኙም በራሱ ላይ ሰልጥኖ በበቀለበት ማኅበር ልማድ ተገዶ የሚሄድበትን የአደን ቦታ በስም ከማወቁ ውጭ እንግዳ ወደ ሆነው ጥቅጥቅ ጫካ ይዘልቃል፡፡ በጀኔፕ የሽግግር ሂደት እና በካምቤል የባህላዊ ጀግና ጉዞ ንድፈ ሐሳቦች የሚታዊ ተጋዳሊውም ሆነ የባህላዊ አዳኙ ጉዞዎች፣ ከወገን መለየት (separation) ተብለው በጋራ ሊጠሩ መቻላቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ በገድል ጥሪዎቹ የሚታዩት የጋራና ተናጠላዊ ጉዳዮች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

4.1.2. እምብኝታ

እምብኝታ ትዕዛዝ ለመፈጸም ፈቃደኛ አለመሆን ነው፡፡ በመለየት ስር ከሚታቀፉት ሚታዊ ተግባራት ከገድል ጥሪ ቀጥሎ የሚመጣው እምብኝታ ነው፡፡ በልዩ ልዩ

መንገዶች የደረሷቸውን የገድል ጥሪዎች በመቀበል፣ ባለመቀበልና እነዚህን ተከትለው በሚመጡት ውጤቶች፣ በሚታዊ ተጋዳሊውና በባህላዊ አዳኙ እጣ ፈንታዎች መካከል ተመሳስሎዎች ይታያሉ፡፡ ሚታዊ ተጋዳሊው የደረሰውን የገድል ጥሪ፣ ‹‹ለእኔ ባይገባኝስ?፣ ባይሳካልኝስ?፣ ጥሪው የመጣው በጎ ካልሆነ ኃይል ቢሆንስ?›› (ቴዎድሮስ 2001፣13) በሚል ተቃውሞና እምቢታ፣ ላለመቀበል በጣም አልፎ አልፎ እምቢተኝነት ሊያሳይ እንደሚችለው ሁሉ፣ በባህል ግፊት የገድል ጥሪ የደረሰው አዳኝም እንዲሁ በጣም አልፎ አልፎ ወደ አደን የማይሄድባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ስለሚኖሩ በተመሳሳይ ሁኔታ በሁለቱም ለእምቢተኝነት የጋራ ጭላንጭል ይታል፡፡

ሁለቱ እምቢተኝነቶች ደረጃዎቻቸው ሊለያዩ ቢችሉም የሚያስከፍሏቸው ዋጋዎች ያሉ መሆናቸውም ያመሳስሏቸዋል፡፡ ለሚት የገድል ጥሪ ‹‹ጆሮን በሰም መጠቅጠቅ፣ ሰምቶ እምብኝ ማለት፣ አልያም እሽ ብሎ ትዕዛዝ አለመፈጸም በረከቱን ወደመርገምት፣ ሲሳዩን ወደ ጥሎሽ፣ ጽድቁን ወደ ኩነኔነት ያስቀይራል›› (ቴዎድሮስ 2001፣13)፡፡ በባህላዊ አደን የባህሉን ግዴታ እንዲወጣ የሚያተጉትን የትንኮሳ ቃል ግጥሞች አለመስማት፣ ማኅበሩ የጣለውን መገለል አምኖ መቀበል፣ ማኅበራዊ ክብርን ወደ ውርደት፣ የአባትነት ማዕረግን ወደ ወላድ መካንነት፣‹‹ተባእትነት››ን ወደ ‹‹እንስትነት›› ይቀይራል፡፡

ለሚታዊ የገድል ጥሪ ምላሽ የነፈገ ተጋዳሊ ጸጋውን ሙሉ በሙሉ እንደሚገፈፈው፣ ጥንካሬውን እያደር እንደሚያጣውና የትም ቢሄድ እንደማያመልጠው ሁሉ፣ ለባህላዊ አደን ጥሪ ትኩረት ያልሰጠ ወንድም የወንድነት ክብሩን ሙሉ በሙሉ ያጣል፤ የባህሉን ግዳጅ በተወጡ ታናናሾቹና የባህል ግዴታ ባልተጣለባቸው ሴቶች በዕድሜው ሊያገኝ የሚገባውን ክብር ይነፈጋል፤ እያደር ይቀላል፤ የዘር ሀረጉን ልማድ ባለማስቀጠሉም የስነልቦና ድቀት ጭምር ይገጥመዋል፡፡

በሁለቱም ለገድል ጥሪ በሚሰጥ የእምቢተኝነት ምላሽ ሳቢያ ከመንፈሳዊ ኃይላትም ይሆን ከማኅበረሰብ የሚሰነዘሩ ቅጣቶች ክብደትና ተቀጪዎቹ እያደር ለከፋ ችግር የሚጋለጡና ከችግሮቻቸው የሚያመልጡባቸው ሌሎች ቀዳዳዎች አለመኖር የልዕለ ተፈጥሮ እገዛን ንኡስ ምእራፍ እንዲጠብቁ ማድረጉም ያመሳስሏቸዋል፡፡

4.1.3. የልዕለ ተፈጥሮ ረድኤት

ለሚታዊ ተጋዳሊው ‹‹መንገዱን የሚጠርጉ፣ ጉዞውን የሚመሩ፣ ልዕለ ተፈጥሯዊ ረዳቶች ... ›› እንዳሉት ሁሉ፣ (ቴዎድሮስ፣ 2001፣15)፡፡ ለባህላዊ አዳኙም፣ መንገዱን ቀኝ የሚያደርጉ፣ እድሉን የሚያሳምሩና ለድል እንዲበቃ የሚያግዙ ኃይሎች ስላሉ ምስስሎሽ ይታያል፡፡

አዳኙ የገድል ጥሪውን ተቀብሎ ከማኅበረሰቡና ከዘወትራዊው ሕይወት ሲለይ በሚኖረው ምርቃት ውስጥ የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታ እንዳለ የሚከተለው መረጃ ያሳያል፡፡

Daacheen qabee sitti haakennu	ዳቼ[4] ይዞ ይስጥህ፣
Kan madda'fi marga fixetti dhaqi	እህል ውሃው ያለቀውን ያጋጥምህ፡፡

አዳኞቹ ባለድል ለመሆን የዱር እንስሳትን ይጠብቃሉ የሚሏቸው የበረሃ አማልክት[5] ዳቼና ጫቶ ታዳኝ እንስሳትን አሳልፈው እንዲሰጧቸው የተለያዩ መለማመኛዎችን እንደሚያቀርቡ በቡድን ተኮር ውይይት የተገኘው መረጃም ያሳያል፡፡

በሁለቱም ልዕለ ተፈጥሮ ረዳቶች ቢኖሩም፣ የሚታዊ ተጋዳሊው ረዳቶች ‹‹ተጋዳሊው አደጋ እንዳይደርስበት ቀድሞ በማስጠንቀቅ፣ በአካል ከተጋዳሊው ጋር በመንዝ፣ ከጠላቶቹ ጋር ፊት ለፊት በመግጠም›› (ቴዎድሮስ፣16) ሲሆን፣ የባህላዊ አዳኙ ልዕለ ተፈጥሮ ኃይሎች እርዳታ የሚገለጸው ለድል የሚያበቃውን ታዳኝ አጋልጦ በመስጠት መሆኑ ያለያያቸዋል፡፡ እንዲሁም የሚታዊ ተጋዳሊው ረዳቶች የመማጸኛ መስዋዕት የማይጠይቁ የአምላክነት ክብር የሚሰጣቸው ሲሆኑ፣ የባህላዊ አዳኙ ረዳቶች መናፍስት (የጅን፣ የዛር፣ የሰይጣን) ወገን መሆናቸው በክብር የተለዩ ያደርጋቸዋል፡፡ ሚታዊ ተጋዳሊም ሆነ ባህላዊ አዳኝ በልእለ ተፈጥሮ እገዛ የመጀመሪያውን ቅጽር ወደመዝለቅ ንኡስ ምዕራፍ መሸጋገራቸው ያመሳስላቸዋል፡፡

4.1.4. የመጀመሪያውን ቅጽር መዝለቅ

ሚታዊ ተጋዳሊውም ሆነ ባህላዊ አዳኙ በልዕለ ሰብ ኃይሎች እርዳታ እየታገዙ ጉዟቸውን የመጀመሪያውን ቅጽር ወደመዝለቅ ሲገፉ፣ ከፊት ለፊታቸው በሚጠብቋቸው ዓለማትና ዓለማቱን በሚጠብቁት ዘቦች ተመሳስሎዎችና ልዩነቶች ይታያሉ፡፡

የመጀመሪያውን ቅጽር መዝለቅ ለሚታዊ ተጋዳሊውም ሆነ ለባህላዊ አዳኙ የገድል ጥሪያቸውን ለመቀበል ፈቅደውና ራሳቸውን አዘጋጅተው ገድል ወደሚፈጽሙበት ቦታ በሚያደርጉት ጉዞ ተመሳሳይ ድርጊቶች ይታያሉ፡፡ ሁለቱም ከአንድ ሥፍራ ወደሌላ ሥፍራ ተጉዘው ድንበር ያቋርጣሉ፤ ‹‹ከነባር ሁናቴ ወደ አዲስ ሁናቴ፣ ከነባር ልማድ ወደ አዲስ ልማድ፣ ከዘወትር ዓለም ልዩ ወደ ሆነ ዓለም ሽግግር ያደርጋሉ፡፡›› ልዩነቱ የሚፈጠረው ሚታዊ ተጋዳሊውና ባህላዊ አዳኙ ገድላቸውን ለመፈጸም በሚዘልቋቸው ዓለማት አይነት ነው፡፡

‹‹በሚት ውስጥ ተጋዳሊው ታላቁን ገድል ለመፈጸም የሚዘልቀው ከሰው ልጆች የመኖሪያ አካባቢ ርቀው ወደሚገኙ፣ ፈጽሞ ወዳልተደረሰባቸው፣ ወይም በወጉ ወዳልታወቁ ጨለማና አስፈሪ ሥፍራዎች ነው፡፡ እነዚህ ሥፍራዎች ጥብቅና … ክልክል ቀጠናዎች ሲሆኑ፣ በየቅጽሮቻቸውም የሚቆሙ ዘቦች … አሏቸው›› (ቴዎድሮስ 2001፣22)፡፡ አዳኞች፣ የአደን ሰለባዎቻቸውን ለማግኘትና ታላቅ ገድላቸውን ለመፈጸም የሚሄዱበት ቦታ፣ ከሰው ልጆች መኖሪያ የራቀ በመሆኑ ከሚታዊ ተጋዳሊው የገድል መፈጸሚያ ቦታ ጋር ቢያመሳስለውም፣ ከዚህ ቀደም

[4] የጎሽ ጠባቂ ተደርጎ የሚታመንበት የበረሃ አምላክ
[5] በሚት ተጋዳሊ የልዕለ ተፈጥሮ እርዳታ እንዳለው ሁሉ በአዳኞችም ይኸው እርዳታ ይኖራል፡፡

ሰው ደርሶበት የሚያውቅ፣ ውስጡም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የሚታወቅ፣ በጥብቅ ያልተከለከለና በጨለማም ያልተከበበ በመሆኑ ይለያል፡፡

ሚታዊ ተጋዳሊውን የሚገዳደሩት ኃይሎች ማራኪ ገጽታን ተላብሰው በማማለል፣ ገጽታቸውን በመለዋወጥ ወይም በተቃራኒዎች ግጥምጥምነት ሲሆን፣ ባህላዊ አዳኙን የሚጻረሩት ኃይላት ፊት ለፊት በቀጥታ የሚያጠቁ እንደወባ፣ እባብና አደገኛ የዱር እንስሳት አይነቶቹ መሆናቸው ያለያያቸዋል፡፡

4.1.5 የመጨረሻውን ቅጽር መዝለቅ

የመጨረሻውን ቅጽር በመዝለቅ ሂደት በሚገጥሙ ከባድ ፈተናዎችና እሱን ተከትለው በሚመጡ ውጤቶችም በሚታዊ ተጋዳሊና በባህላዊ አዳኝ ዕጣዎች ተመሳስሎዎችና ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ ለሚታዊ ተጋዳሊው የመጨረሻውን ቅጽር መዝለቅ ‹‹ታላቅ በረከት›› ከ‹‹ታላቅ ጻዕር››ጋር ተጣምረው እንደሚጠብቁት ሁሉ፣ ለባህላዊ አዳኙም የ‹‹ሰለባ በረከት›› በ‹‹በታዳኙ ህይወትን እስከመነጠቅ ከሚያደርሱ መቅሰፍቶች›› አድፍጠው ስለሚጠብቁት፣ የሁለቱም እጣዎች ይመሳሰላሉ፡፡ የሚለያዩት፣ ሚታዊ ተጋዳሊው በሚጋፈጣቸው የመጨረሻ ቅጽር ጠባቂዎች ቢማረክ፣ በግዙፋን ቢዋጥና በመቃብር ቢሸበብ፣ በሰርኩም ይባል በእንግዳው ዓለም ላይ የሚሰለጥንና ለድል የሚበቃ ሲሆን፣ አዳኙ ከቅጽር ጠባቂዎቹ በአንዱ ለምሳሌ በዘንዶ ቢዋጥ፣ በእባብ፣ በወባ ተነድፎ ወይም ለግዳይ ባቆሰለው ጎሽ፣ አንበሳ፣ ዝሆን ተጠቅቶ ቢሞት፣ ወደአዲሱ ዓለም የማይሻገርና በሰርኩ ዓለምም እንደወጣ ቀሪ ተራ ሟች መሆኑ ነው፡፡

በተጨማሪም፣ ሚታዊ ተጋዳሊው ጻሩን የሚያልፈው አንዴ ሲሆን፣ ባህላዊ አዳኙ ግዳይ በመጣሉና የዚሁ ማስመስከሪያ ሰለባ በመያዙ የመጨረሻውን ቅጽር ከመዝለቅ ይልቅ፣ ለዳግም መነጠልና ለሌላ የከፋ አደጋ የሚዳረግ መሆኑም ያለያያቸዋል፡፡ አዳኞቹ ተራ ገብተው ሲያድኑና አንዱ ሲቀናው ጎጆ ተሰርቶለት ከሌሎቹ አዳኞች እንደገና ተነጥሎ (double liminality) ጠባቂዎች ተመድበውለት ይቀመጣል፡፡ ሌላ አዳኝ ቡድን ካገኘው ሰለባውን ሊነጥቀው፣ ሲከፋም ሊገድለው ስለሚችል ለሁለተኛ ጊዜ ለአስጊ አደጋ ይጋለጣል፡፡

ሚታዊ ተጋዳሊው ‹‹እውነተኛ ተጋዳሊነቱ›› ይረጋገጥ ዘንድ ወደነዚህ የአደጋ ቀጠናዎች በድፍረት ዘልቆ ከባድ መስዋዕትነቶች ከፍሎ ከበረከት ጋር ወደ ተለየው ማኅበር እንደሚመለሰው ሁሉ፣ (ገጽ፣37) ባህላዊ አዳኙም ‹‹እውነተኛ አዳኝነቱን›› ለማረጋገጥ ታዳኞቹ ወደሚገኙበት ጥቅጥቅ ጫካ ዘልቆና ራሱን ለአደጋ አጋልጦ በሚከፍለው መስዋዕትነት የድል ማሳያ የሆነውን የፋቻ (የሰለባ) በረከት ይዞ የሚመለስ በመሆኑ ይመሳሰላሉ፡፡

የባህሉን አጥር ጥሶ በገድልና በተዓምር በተሞላ መንገድ የሚጓዘው ሚታዊ ተጋዳሊና የባህሉን አጥር ለማጥበቅ በውጣውረዶች በተሞላ መንገድ የሚጓዘው ባህላዊ አዳኝ በወጡበት ማኅበረሰብ ላይ የሚፈጥሩት ስሜት ቢያለያያቸውም፣ ጉዟቸውን በድል ሲያጠናቅቁ ግን ለራሳቸው በሚቋደሷቸው ብቻ ሳይሆን፣

ለወገኖቻቸው በሚያስገኟቸው የድል በረከቶች ተመሳስሎዎች ይታያሉ፡፡ ሚታዊ ተጋዳሊው ‹‹ … ከዚህ የሞት ሽርት ትግል በኋላ ይህ ሰው የወትሮው ሰው አይሆንም›› (ቴዎድሮስ 2001፣ 29)፡፡ ባህላዊ አዳኙም በበርሃው የሞት ሽረት ትግል ግዳይ ጥሎ ወደ ትውልድ መንደሩ ሲደርስ፣ ባለድልነቱን እየገለጸ የሰፈሩ ልጃገረዶች በደስታ እንዲቀበሉት ጌረርሳውን ሲሸልል የዱሮው ሰው አለመሆኑን፡-

Sirbaa kaa yaa dubaree	ዝፈኑ ልጃገረዶች፣
Dubaree goodaa buree	የቡሬ መንደር ልጆች፡፡
Arka koo duwwaa miti	ባዶ እጄን አልመጣሁም፣
Akka koo duraas mitii	እንደ ዱሮም አይደለሁም፣
Faachi mirga gafarsaa	ፋቻ የጎሽ ገዳዩ ምልክት፣
Maddii namaa magarsa	ጉንጫም ያደርግሃል፣(ያወዛል ፊት)፡፡

እያለ የሽግግሩን ስኬት ያውጃል (ቃለመጠይቅ፣ ቡሬ ወረዳ 8/9/2010 ዓ.ም)፡፡

ሚታዊ ተጋዳሊውና ባህላዊ አዳኙ ወደግቦቻቸው ለመድረስ የሚያልፏቸውን ድንበሮች ሲዘልቁ በሚያገኙት የድል አድራጊነት እውቅና ልዩነቶች ይታሉ፡፡ የመጨረሻው ቅጽር ጠባቂ ዘቦች ‹‹ለሰብእና ውላጤ…ለተዘጋጀ፣ ለበቃ፣ ለደፈረ.›› ሚታዊ ‹‹ተጋዳሊ ብቻ ‹ይለፍ› ይሰጣሉ፡፡›› (ገጽ፣ 40)፡፡ ድንበሩ እንደታለፈ የድል አድራጊነት እውቅና ይሰጣል፡፡ የአዳኝነት ማኅበራዊ ክብርን ለማግኘት የቆረጠ አዳኝ ከቅጽር ጠባቂ ዘቦቹ ‹‹ይለፍ›› የሚያገኘው፣ በቆራጥነቱ ብቻ ሳይሆን በእድል ጭምር በመሆኑ ከሚታዊ ተጋዳሊው ዕጣ ይለያል፡፡ ሚታዊ ተጋዳሊው በብርቱ ተጋድሎው የመጨረሻውን ቅጽር ዘልቆ ግቡ የሆነውን ልእለ ሰብዕናን ለመጎናጸፍ ምስክር መቁጠር አይጠበቅበትም፡፡ ባህላዊ አዳኙ ግን የአዳኝነትን ማኅበራዊ ክብር ለመጎናጸፍ ገድሉን ሲፈጽም የነበሩትን እማኞች መጥራትና በሥርዓቱ በተሰበሰበው ህዝብ ፊት የምስክርነት ቃላቸውን ማግኘት ይጠበቅበታል፡፡ እነማን ባሉበት እንደገደለ፣

Bu’een boora leejjisee	ወርጂ ገራሁ ጎሹን፣
Baayoo Mootii biratti	ባዮ ሞቲ ባለበት፣
Warqee Dirroo birattii	ወርቁ ድሮ ባለበት፣
Abbuu Saaqaa biratti	አቡ ሳቃ ባለበት፣
Bakkee Garree biratti	በኬ ገሬ ባለበት፣
Dhaabbadheen dhaabbachiisee	ይኼው ቆሜ አቆምኩት፣

እያለ ሲሸልል በስም ተጠቃሽ የአደን ጓዶቹ እውነት መሆኑን ይመሰክራሉ፡፡ (ኪረሙ ቀበሌ የቡድን ውይይት፣ ሚያዝያ 2010 ዓ.ም)

ባህላዊ አዳኙ፣ በሌላ ያልቆሰለውን፣ ሮጦ ማምለጥና ተቆጥቶ አደጋ ማድረስ፣ የሚችለውን እንጂ የታመመውን ወይም ሙቶ ያገኘውን የዱር እንስሳ ሰላባ ይዞ ያልተመለሰ መሆኑን፣ አብረውት የነበሩት ጓደኞቹ ለስርዓቱ ተሳታፊዎች የምስክርነት ቃላቸውን እስከሚሰጡ ድረስ፣ ወደሚቀጥለው ማኅበራዊ ደረጃ (የመጠቃለል ምእራፍ) አይሸጋገርም፡፡ ይህም የመጨረሻውን ቅጽር እንደዘለቀ የተነሳበትን ግብ ከሚያሳካው ሚታዊ ተጋዳሊ የተለየ ያደርገዋል፡፡ ሚታዊ ተጋዳሊውም ሆነ ባህላዊ አዳኙ ከፍ ሲል እንደተገለጸው፣ በየራሳቸው ማረጋገጫ

ቅጽሩን አልፈው ወደውስጥ ሲዘልቁ፣ የትናንት ማንነታቸው ጠፍቶ፣ በአዲስ ማንነት ዳግም በመወለዳቸውም ይመሳሰላሉ፡፡

በዳግም ልደታቸው ግብ ግን ይለያያሉ፡፡ ቴዎድሮስ (2001) እንደሚገልጹት፣ የሚታዊ ተጋዳሊው ዳግም ልደት ‹‹ግብ በተፈጥሮ መላቅ፣ ልእለ ሰብእናን መጎናጸፍ፣ በዚህም የዓለም ማዕከል፣ የዓለም እምብርት መሆን…›› (ገጽ፣ 40) ሲሆን፣ የባህላዊ አዳኙ ግብ በተመሳሳይ ሂደት አልፈው ማኅበራዊ ክብር ወዳገኙት ባህላዊ አዳኞች መጠቃለል ስለሆነ፣ በሁለቱ ግቦች መካከል ልዩነቶች ይታሉ፡፡

ሚታዊ ተጋዳሊውም ሆነ ባህላዊ አዳኙ ከድል መልስ ለወገኖቻቸው በረከት ይዘው በመመለስና በታሪክ ሲዘከሩ በመኖራቸው ዙሪያ ተመሳስሎና ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ ሚታዊ ተጋዳሊው ‹‹… መከራን ከተቀበለበት ሥፍራ ለወገኖቹ የሚሆን በረከት … ይዞ ይመለሳል፡፡ …ወገኖቹም የዕርሱን ፈለግ ይከተላሉ፡፡ ገድሉም ለዘላለም በአንደበታቸው ሲወሳ ይኖራል፡፡›› (ቴዎድሮስ 2001፣30)፡፡ እንዲሁ ሁሉ፣ ባህላዊ አዳኙም ለሚስቱ ክብርን፣ ለወላጆቹ ሞገስንና ለዘሩ ወንድነትን (ጀግንነትን) ይዞ ይመለሳል፡፡ ታሪኩም በሚተክለው ፋቻ በስሙ መጠሪያነት ሲዘከር ይኖራል፡፡

የሚታዊ ተጋዳሊው ተጋድሎ ሃይማኖታዊ ከሆነ፣ በገድል መጽሐፍ ሲተረክ፣ የአዳኙ ጀግንነት መንገድ ዳር በሚተከል ፋቻና በእሱ ዙሪያ አድገው በስሙ በሚጠሩት ዛፎች ስለሚተላለፍ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ የሚታዊ ተጋዳሊውም ሆነ የባህላዊ አዳኙ ድሎች ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ለወገን አንዳች በረከት በማስገኘት ብቻ ሳይሆን፣ ድሎቹ ለሌላ አካል የማይወረሱ በመሆናቸውም ይመሳሰላሉ፡፡ ሚታዊ ተጋዳሊው ለወገኖቹ ነጻነትን በማስገኘቱ ሲዘከር፣ ባህላዊ አዳኙ የዘር ሐረግን ጀግንነት በማስቀጠል በወገኖቹ ሲወደስ ይኖራል፡፡ የሚታዊ ተጋዳሊውን ድል ሌላው ወርሶ የራሱ ማድረግ እንደማይችለው ሁሉ፣ የባህላዊ አዳኙንም የጀግንነት ክብሩን እሴት ወኪሎች፣ በቅርበት የምትካፈለው ሚስቱና ልጆቹ የማይወርሱ መሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡

Jiruu gootaatu akkanaa	የጀግና ተግባሩ እንዲህ ነው፣
Gurra tokkotti tootii	ባንድ ጆሮዬ ሎቲ፣
Gurra tokkotti warqii	ወርቅ በሌላው፣
Kan namaa hinlaanne haadhoon	ወንድምም የማይወርሰው፣
Kan sanyoo hin laanne niitiin	ሚስት ለውሽማዋ የማትሰጠው፡፡

እያለ ግዳይ እንደጣለ የሚሸልለው ጌረርሳ የሚያሳየው ይህንኑ ነው፡፡

Vogler (2003) በሚታዊ ጀግናና በፊልሞች ገጸባህርያት የታሪክ ጉዞ ምእራፎች ንጽጽር እንዳረጋገጡት፣ ጀግኖቹ ዓላማዎቻቸውን ለማሳካት የሚያልፉባቸው ጉልህ የጉዞ ምእራፎች አካላዊ ብቻ ሳይሆኑ ስሜታዊና ስነልቦናዊ እንደሆኑት ሁሉ የአዳኙም ተመሳሳዮች ናቸው፡፡ ሚታዊ ተጋዳሊው የጥሪ ገድሉን ተቀብሎ ወደማያውቀው እንግዳ ዓለም ሲንቀሳቀስ በአካል ብቻ ሳይሆን በስሜት ወይም

በስነልቡና ያንን ጉዞ ለማድረግ በሚያስችል ደረጃ ዝግጁነት እንደሚፈጥረው ሁሉ፣ አዳኙም ከባህል በታጠቀው ተመሳሳይ የሥነልቡና ዝግጅት ያደርጋል፡፡

5. የውጤት ማብራሪያ

በገለጻው ክፍል ጀግንነት እንደየባህሉና እንደየዘመኑ አስተሳሰብ ሊተረጎሙ የሚችሉ የተለያዩና ሰፋፊ ሐሳቦችን የያዘ ጽንሰ ሐሳብ መሆኑን (Goldberg፣ 2009) እንደገለጹ ተጠቅሷል፡፡ ስለጀግንነት ከተሰጡት በርካታ ብያኔዎች መካከል ለሚታዊ ተጋዲሊና ለባህላዊ አዳኝ የሚስማሙት፣ ‹‹ከምሥጢራዊ ዓለም ለወገኖቹ (ተከታዮቹ) ክብር ከሚያስገኝ በረከት ጋር የተመለሰ›› (Campbell (2004 [1949]) እና ‹‹… ወኔ፣ ድፍረት በሚጠይቅ ሁኔታ ላይ ጀብዱ የሰራ፣ ብርታት፣ ጥንካሬ የሚጠይቅ ሥራ ላይ ችግርን ተቋቁሞ ለውጤት የበቃ ጎበዝ›› (አማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣488)) የሚሉት ብያኔዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ Propp (1984፣149) በሶቪየት የጀግና መወድሳዊ ግጥም (ኢፒክ) ትግልና ድል በመሠረታዊ ይዘትነት መነሳታቸውን ከገለጹት ጋር በሚስስማማ መልኩ በሚታዊ ተጋዳሊና በባህላዊ አዳኝ ይዘቶችም ተመሳሳይ ጉዳዮች መነሳታቸውን መረጃዎች አሳይተዋል፡፡ የሁለቱም የጉዞ ምዕራፍ መዋቅሮች Vogler (2003) በሚታዊ ጀግናና በፊልሞች ገጸባህርያት የታሪክ ጉዞ ተመሳስሎ መኖሩን ካሳዩበት ጥናት የሚስማማ ውጤት ተመዝግቧል፡፡

ለዘመናችን እውነታ ዘይቤያዊ መገለጫ የሆኑ ተረኮች *(የፊልሞች ገጸባህርያት ገድሎች)*[1]፣ የነባሮቹ ሚታዊ ተረኮች አምሳያዎች መሆንና … (ቴዎድሮስ፣ 89) በባህላዊ አዳኝ ጌረርሳዎቹም ይኸው እርሾ መኖር፣ የሁለንተናዊነት ጉዳይ በጊዜና ቦታ ሳይገታ መቀጠሉን ያሳያል፡፡

በኢሴንሻሊዝም ፍልስፍና፣ የግለሰብም ሆነ የቡድኖች ርዕዮተ ዓለሞችና እነዚህን ለማጽናት የሚፈጠሩት ባህላዊ እሴቶች በተፈጥሮ የሚወረሱና ዘላቂነት ያላቸው ተደርገው መወሰድ፣ የጀግንነት እሴቶችም በዚሁ ትይዩ እንዲታዩ ቢያደርጉም፣ ከዚህ በተቃራኒ በቆመው ድኅረ ዘመናዊ አንጻራዊነት ፍልስፍና ርዕዮተ ዓለማዊ እሴቶች በወጥነት ሳይሆን በተለያዩ አማራጮች ሊመረመሩ የሚገባ መሆኑ፣ የጀግንነት እሴቶች እንደየባህሉና እንደያውዱ በተለያዩ መንገዶች ሊበየኑ እንደሚጋባ ያሳያል፡፡

የእነዚህ ፍልስፍናዎች ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በብሉይ ሚቶሎጂና በሀዲስ ሚቶሎጂ መሃከል በግልጽ መታየቱ፣ እነዚህን ተከትለው በተፈጠሩት ነባርና አዳዲስ የባህላዊ አዳኝ ተረኮች ውስጥም ተጠባቂ ያደርጋቸዋል፡፡ አዲሱ ተጋዳሊ ከቀደምቱ ተጋዳልያን እንደሚቀዳው ሁሉ፣ አዲሱ አዳኝም ከነባሩ አዳኝ የቀዳቸው ባህርያት በውስጡ ይኖራሉ፡፡ አዲሶቹ ተረኮች ነባሮቹ እሴቶች ባደሩባቸው ቀደምት ተረኮች እርሾነት የተበጁ መሆን፣ የባህላዊ አዳኙ ጌረርሳዎችም ከባዶ የሚጀምሩ ወይም ከቀዳሚዎቹ የሚፋቱ አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡

ይህም ቴዎድሮስ (2001፣76) Leemingን (2002) ዋቢ በማድረግ ‹‹ሁሉም ባህል ከኃይማኖትና ከክብረ በዓላት ጋር የተዛመዱ ነባር ሚቶችን ከዘመኑ መንፈስ ጋር

አስማምቶ እያበለጸገ የሚያዘልቅበት፣ በአዲስ በቀል ፍልስፍና ርዕዮተ ዓለምና ዕውቀት አማካይነት አዳዲስ ሚቶችን ከ‹‹ዛሬ›› አብራክ የሚያፈልቅበት ቋሚ ሥርዓት እንዳለው›› ከገለጹት ጋር ይስማማል፡፡

የኢሴንሻሊዝም ፍልስፍና እና የዘመናዊነት የኪነጥበብ እንቅስቃሴ፣ በሁለንተናዊ እውነታ ማመን፣ የድኅረ ዘመናዊ አንጻራዊነት ፍልስፍና በእውነታ ተለዋዋጭነት፣ ግለሰባዊነትና ሁኔታዎች ላይ ተመስራችነት ላይ ማትኮር፣ በሁለቱ ፍልስፍናዎች መሃከል መሠረታዊ ተቃርኖ መኖሩን ብቻ ሳይሆን፣ የመጀመሪያዎቹ ለሁለንተናዊነት፣ ሁለተኛዎቹ ለአካባቢያዊነት ትኩረት የሚሰጡ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

ወደ ጉዞዎቹ ተመሳስሎ ስንመለስ፣ በመለየት ዋና ምእራፍ ስር በሚገኙት አምስት ንዑሳን ምዕራፎች (በገድል ጥሪ፣ ጥሪውን ለመቀበል በሚኖር ፈቃድ (እምብኝታ)፣ በልእለ ተፈጥሮ ረድኤት፣ የመጀመሪያውን እና የመጨረሻውን ቅጽሮች በመዝለቅ) በሚታዊ ተጋዳሊውና በባህላዊ አዳኙ የዕጣ ጉዞዎች መካከል የተደረጉት ንጽጽሮች ተመሳስሎዎች (ሁለንተናዊነቶች) መኖራቸውን አሳይተዋል፡፡

እነዚህ የዕጣ ጉዞ ተመሳስሎዎች በLévi-Strauss (1981) ከሰው ልጅ የአእምሮ መዋቅር መመሳሰል ወይም Bascom (1954) የፎክሎርን ተግባር፣ የማስተማር፣ የመትከል፣ የመቆጣጠርና የማምለጥ አድርገው ለሁሉም ባህሎች እንደሚሰራ እንዳሳዩት፣ መረጃዎቹን በሰፊ መነጽር ከመመልከት ሊመጡ እንደቻሉ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በፎክሎር መረጃ ትንተና እንዲህ አይነቱ ተመሳስሎ ላይ ብቻ ማትኮር፣ በአንድ ባህል የሚገኙ መረጃዎች ለሌላ ባህል በወጡ መስፈርቶች እንዲታዩ ማድረግን በማበረታታት፣ በዚያ መስፈርት የማይገቡት ጠቃሚ መረጃዎች ባክነው እንዲቀሩና እነዚህ መረጃዎች በመባከናቸው ወይም ችላ በመባላቸው አዳዲስ ዕውቀቶች ወደአካዳሚው መድረክ ሳይገቡ እንዲቀሩ ያደርጋል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው በታሪክ ጉዞ መዋቅርም ይሁን በሚነሱት ይዘቶች ሁለንተናዊነት ቢታይም፣ ማኅበረሰቦችን በሚገጥሟቸው ተግዳሮቶች መለያየትና ተጋዳሊው/አዳኞቹ ተግዳሮቶቹን ለመፍታት በሚከተሏቸው ባህላዊ መርሆዎች የተነሳ ልዩነቶች መኖራቸውን ከሚያሳየው የLowrey (2009፣1) የጥናት ውጤት ጋርም የዚህ ጥናት ውጤት ይስማማል፡፡

በንጽጽሩ የተገኙት ዝርዝር መረጃዎች በግልጽ እንዳሳዩት፣ በአምስቱም የመለየት ንኡሳን ምእራፎች፣ በሚታዊ ተጋዳሊና በባህላዊ አዳኝ የዕጣ ጉዞዎች ውስጥ ባህል ፈጠር ልዩነቶች ተስተውለዋል፡፡ በገድል ጥሪ ንኡስ ምእራፍ ብቻ እንኳ፣ ለባህላዊ አዳኙ የገድል ጥሪ የሚደርሰው አብረውት በሚኖሩት መሰሎቹ መሆኑ፣ የገድል ጥሪው ወንድ ሁኖ በመወለድ የባህል ሕግ አስቀድሞ መወሰኑ፣ ለገድል የመጠራቱ ምክንያት ማኅበሩ ለማስቀጠል የሚፈልገውን ባህል እንዲያስጠብቅ መሆኑ፣ ጥሪ የሚደርሰው በወገኖቹ ልማዳዊ ግፊት መሆኑ፣ ለጥሪው እምቢታ የሚጠብቀው

ቅጣት ከሚታዊ ተጋዳሊው ቀለል ያለ መሆኑ፣ የባህላዊ አዳኙን የገድል ጥሪ አካባቢያዊ ያደርጉታል፡፡ በመረጃ ትንተና እንዲህ አይነት ልዩነቶች ላይ ብቻ ቢተኮር ኖሮ፣ ቀደም ሲል በንጽጽሩ በሚታዊ ተጋዳሊው ጉዞ የታዩትን ሰው በመሆን የዳበሩትን ሁለንተናዊ የጋራ ጉዳዮች መዘንጋትን ያስከትል ነበር፡፡ ይህም የጋራ ሰፊ አካዳሚያዊ ዕውቀትን የመገንባት ዕድሉን ያቀጭጫል፡፡

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ፣ የዚህ ጥናት ውጤት የፎክሎርን ብሄርተኝነትና የወደፊት ተግዳሮቱን የመረመሩት አብርሃም (1994፣149) ከእኛ ባህል ውጭ የሆኑ የሌሎች ባህሎችን ስናነጻጽር የሚያለያዩን ገጽታዎች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ሰው ሆኖ በመወለድ በጋራ የሚያስተሳስሩን ላይም ማትኮር እንደሚገባ ከገለጹት ጋር ይደጋገፋል፡፡ የፎክሎር መረጃዎች ባለቤቶቻቸውን በሚገባ ለመረዳት ቢያስችሉም፣ በትንታኔያችን ከሰው ልጅ የጋራ ልምድ መመንጨታቸውን ሳንዘነጋ የጋራ ጉዳዮችን ማሳየት እንደሚገባ ከሚያስገነዝበው ግኝት ጋርም ይጣጣማል፡፡ በዚህ ረገድ በሁለንተናዊና በአካባቢያዊ የፎክሎር ንደፈ ሐሳቦች አጠቃቀም ዙሪያ የተደረጉ ክርክሮች ዕውቀትን በማድበስበስ ያላቸውን አንድምታ የመረመሩት Fine (2008)፣ የሁለቱንም ጠንካራና ደካማ ጎኖች በውል ተገንዝቦ በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ ከደረሱበት ድምዳሜ ጋር የዚህ ጥናት ውጤት ይደጋገፋል፡፡

በአጠቃላይ በሰፊው የሚመሳሰሉ ልዩ ልዩ የጀግና ጉዞዎች፣ በዝርዝር ጉዳዮች ልዩነት የሚታይባቸው የሚታዊ ተጋዳሊና የባህላዊ አዳኝ ዕጣ ጉዞዎች፣ ሚቶቹና ባህሎቹ ከተገኙባቸው ማኅበረሰቦች ርዕዮተ ዓለም፣ ከአካባቢ እና የእነዚህ ድምር ውጤት ከሆነው ባህል የመነጨ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

በይነ ዲሲፕሊናዊነት የባህሪው በሆነው ፎክሎር ሁለንተናዊ ጉዳዮች የመኖራቸውን ያህል፣ የአንድ ፎክ ቡድን የጋራ ሎር ውስጥ የሚደረገው ትርጉም ፍለጋ፣ የቡድኑን አባላት፣ እድሜ፣ ጾታ፣ ማኅበራዊ ደረጃ፣ የተነገረበት አውድ፣ የቡድኑ አባላት ለሎሩ ያላቸውን ግለሰባዊ ልምድና ትርጉም የመፈለግ ሂደት ወዘተ. ሲታዩ፣ የሚገኘው ትርጉም የተለያየና ቋሚነት የማይታይበት ይሆናል፡፡ አካባቢያዊነት እንዲህ አይነት ዝርዝር ጉዳዮችን በቅርበት ለማየት ጉልህ ሚና ይጫዎታል፡፡

ስለሆነም ፎክሎራዊ መረጃዎች ሲተነተኑ እነዚህን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ለተለየ ዓላማ አንዱን ለማሳየት ካልተፈለገ በስተቀር፣ የሰውን ልጅ የጋራና የባህሎችን የየግል ባህርያት መሠረት ያደረጉ ሚዛናዊ ትንተናዎችን ማካሄድ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በመጨረሻም በRank (2015፣2) እና በEvans (2018፣12) የጥናት ውጤቶች እንደተረጋገጡት፣ የሚታዊ ተጋዳሊና የባህላዊ ጀግና የዕጣ ጉዞ ተመሳሳይነት፣ ቀደምቱ ሚታዊ ታሪኮች ለኋለኞቹ የሀገራዊ ጀግና ትረካዎች መሠረት በመጣላቸው ስለመሆን አለመሆኑ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ወደፊት በዚህ ዘርፍ ጥናት ቢካሄድ የሚታዊ ተጋዳሊና የባህላዊ ጀግና እጣ ጉዞዎችን ተመሳስሎ ምንጮች በበለጠ ለመረዳት ያስችላሉና ትኩረት ቢሰጥ መልካም ይሆናል፡፡

ዋቢዎች

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ 2001፡፡ በይነዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ፤ሥነጽሑፍ እና ሚቶሎጂ፣ ፍልስፍና፣ ስነልቡና፡፡ አዲስ አበባ፣ አአዩ ፕረስ፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡፡ (1993)፡፡ ኣማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

Bartels, L. (1983). *Oromo religion: myths and rites of the Western Oromo of Ethiopia, an attempt to understand* (Vol. 8). https://www.jstor.org/stable/40460901.

Bascom, W. R. (1954). Four functions of folklore. *The Journal of American Folklore*, *67*(266), 333-349.

Childs P., & Fowler, R. (2006). The Routledge dictionary of literary terms. Routledge. Taylor & Francis e-Library.

Campbell, J. (2004). The Hero with A Thousand Faces. [1949]. *London: Princeton University Press.*

Elaati, A. (2016). Postmodernism theory. Research Gate, 1-6. http://www.researchgate.net publication.

Evans, R. E. (2018). The mythological perspective of modern media: Cross-cultural Consciousness and modern myths. [Doctoral dissertation, James MadisonUniversity].

Fine, G. A. (2008). The sweep of knowledge: The politics of grand and local theory in folkloristics. *Journal of Folklore Research*, 11-18.

Finnegan, R. (2012). *Oral literature in Africa* (p. 614). Open Book Publishers.

……. (1992). *Oral traditions and the verbal arts: a guide to research practices*. Routledge.

Folklore, Nationalism, and the Challenge of the Future (1994) in the marrowof human experience Wilson, W. A. (2006). The Marrow of Human Experience. Utah State University Press.

Goldberg, L. (2009). The Hero's Journey: Tracing the History of the Myth to the Celebrity. *MA Major Research Paper. Toronto: Ryerson University-York University*.

Green, T. A. (Ed.). (1997). *Folklore: an encyclopedia of beliefs, customs, tales, music, and art* (Vol. 1). Abc-clio. Library of Congress.

Grimes, R. L. (2000). *Deeply into the bone: Re-inventing rites of passage* (Vol. 1). Univ of California Press.

Holm, J., & Bowker, J. (Eds.). (1994). *Rites of passage*. A&C Black.

Jayawickreme, E., & Di Stefano, P. (2012). How can we study heroism? Integrating persons, situations and communities. *Political Psychology*, *33*(1), 165-178. https://www.researchgate.net/

Klapp, O. E. (1954). Heroes, villains and fools, as agents of social control. *American sociological review*, *19*(1), 56-62.

Levi-Strauss, Claude. 1981. *The Naked Man, Introduction to a Science of Mythology,* vol 1.New York: Harper & Row.

Lowrey, B. (2009). The Hero as a Reflection of Culture. *Sabiduria: The Honors College Journal*, *1*(1). https://www.palmbeachstate.edu

Potgieter, F., & Van der Walt, J. (2015). Postmodern relativism and the challenge to overcome the" value-vacuum". *Stellenbosch theological journal*, *1*(1), 236-254.

Propp, V.I. (1984). Theory and History of Folklore. Edited with an introduction and notes by Anatoly Liberman. Translated by Ariadna Y. Martin et al. Theory and History of Literature, vol. 5. Minneapolis: University of Minnesota Press.

Rank, O. (2015). *The myth of the birth of the hero: A psychological exploration of myth* JHU Press.

Roth, A. L. (1995). "Men wearing masks": Issues of description in the analysis of ritual. *Sociological Theory*, 13, pp. 301-327.

Sassower, R. (2018). Postmodern relativism as enlightened pluralism. Relativism and Post-Truth in Contemporary Society: Possibilities and Challenges, 35-52.

Sims, M., & Stephens, M. (2011). *Living folklore: An introduction to the study of people and their traditions*. University Press of Colorado.

Wilson, William A. 1988. "The Deeper Necessity: Folklore and the Humanities. *Journal of American Folklore* 101 (400): 156–67. https://www.jstor.org › stable.

Van Gennep, A. (2013 [1960]). *The rites of passage*. Routledge. University of Chicago press.

Vogler, C. (2003). Excerpts from myth and the movies, Stuart Voytilla: Foreword.www.tlu.ee/rajailed/montaazh/Hero's%2Journey%20Arch.pdf